ሰኔ 16ቀን 2012 (June 23 2020)

# <u>ጀኔራል አሳምነውና የብአዴን አመራሮች አቋማቸው አንድ ነበር እንዴ?</u>

እንደሚታወቀው ከ1983ዓም ጀምሮ ትነግና አነግ ሌሎቹንም ሰባስበው፣ አማራውን በማግለል፣ የአማራን ማጥፊያ ሽግግር መንግሥት በማቋቋምና ህገ መንግሥት ተብዬውን በማፅደቅ፣ ኢሕአዴግ/ብልፅግና የሚል ድርጅታዊ ሥርዓት ፈጥረው እሥከዛሬዋ ዕለት ድረስ መፈናፈኛ እንዳሳጡን አላውቅም የሚል አማራ አይኖርም፡፡

የአማራው ሕዝብ ይህንን ግፈኛ ሥርዓት በመጋፈጥ ትግሉ ገፍቶ መጥቶ ሥርዓቱን ሲያስጨንቀው ቢቆይም፣የሥርዓቱ ብልጣብልጦች ብአዴንን ጨምሮ <u>"አጥፍተናል፣ይቅርታ"</u> ከማለትም አልፈው "አቢይን መረጥን" አሉን፡፡

በማግሥቱ ከአቢይ "የኢትዮጵያ አንድነት ዲሥኩር" ባሻገር፣ በትግሬው አመራር የታሠረውን እሥረኛ የጋላው አመራር ሲፈታ፣በትግሬው አመራር የተባረረውን፣በጋላው አመራር "ከዬትም ያለህ አገርህ ግባ ወዘተ" ሲባል፣ "የአማራው ሕዝብ! በጊዜያዊ ግርግር ተዘናግቶ የራሱን ትግል አሸንፕሮ ጥሎ የአቢይ ደጋፊ ሆነ፡፡እነአቢይ ይህን ወቅት የተጠቀሙበት "<u>ለጊዜ መግዣ</u>" ሲሆን ፣ከአሥራት ሜዲያ ጀምሮ የሚንቀሳቀስ አማራ ደግሞ "<u>ለውጥ</u>" እያለ ሲናገር እገረማለሁ፡፡

ይህ ከትግሬ ወደ ጋላ የተደረገ የሥልጣን ሽግሽግና የድርጅት ሥም ለውጥ እንጅ የኢሕአዴግ/ብልፅግና ሥርዓትና ህገ መንግሥት አልተለወጠም፡፡አማራው የታገለው ደግሞ ሥርዓቱን ከእነህገ መንግሥቱ ለመለወጥ ነበር፡፡፡

ከሠኔ 15/16ቱ ክስተት በፊት፣ አቢይ "ጊዜ የገዛበትን" እና ትክክለኛ ማንነቱ ከታወቀበትም በኋላ ያሉትን ጊዜያት፣አማራው! እንደጀኔራል አሳምነው ዓይነት የአማራው ችግር በጥልቀት የገባው ሠው በማግኘቱ ጭምር ፣ከተዘናጋበት ነቅቶ የኢሕአዴግ/ ብልፅግናና የመሠል ጠላቶችን ማነቆ በማለፍ፣ የአማራውን ትግል ለማጎልበትና ለህልውናው ብቃት እንዲኖረው ለማሥቻል ከጊዜ ጋር በመሮጡ ትግሉ እየጎመራ መምጣት ጀምሮ ነበር፡፡

በዚህ መልክ ይህንን እየተሰራብን ያለውን የማያባራ ሤራ ከመነሻው ጀምሮ ለማስታዎስ ይረዳን ዘንድ ጠቅለል ባለመልኩ አቅርቤዋለሁ፡፡ አሁን ወደዋናው የዛሬው ርዕስ ልግባ!

በቅድሚያ ጀኔራል አሳምነው የደረሰበትንና አንዳንድ የተናገራቸውን ልጥቀስ፣

-በመከላከያ አመራር በነበረበት ወቅት ንቃት ሥለነበረው ፣በትነግ ጊዜ ከተናገራቸው መካከል አንዱ "እነከበደና ገመቹ የት ሄደው ነው እነጎይቶም የበዙት?" ያለ ጀግና ነው ፡፡

-ፀረ አማራ የሆነውን "ህገ መንግሥት በመናድና በሽብር ተብዬው" ተከሰና ታሥሮ እንደተፈታም ይታወቃል፡፡

-በአንድ ወቅት በአንድ ስብሰባ ላይ "ሽምግልና የሚሉትን ሠዎች ትክክለኛ ሽማግሌዎች ሁኑ፣ የሀይማኖት አባቶችም እንደአቡነ ጴጥሮስ ሁኑ፣እሥከማለት ደርሷል፡፡

ይህንን ካልኩ በኋላ፣ **<u>ጀኔራል አሳምነው! ከእስር ከተፈታ በኋላ "እየተለወጠ ነው" ወደተባለለት ብአዴን| አዴፓ (የኢሕአዴግ/ ብልፅግና) መጥቶ ሲቀላቀል ምን አለ? ምንስ ተናገረ? መቶ በመቶ በብአዴን| አዴፓ (በኢሕአዴግ/ ብልፅግና) አቋም አምኖበት ነበር? ወይስ ጥርጣሬውን አሥቀድሞ ተናግሯል? እነኝህ ወሳኝና ቁልፍ ጥያቄዎች መልስ ያሻቸዋል</u>**፡፡ አሁን ወደዝርዝሩ!

(ሀ) “በቀደመው የብአዴን ድርጅት ውስጥ ሰዎች በዴሞክራሲና በነፃነት ሀሳባቸውን የሚያራምዱበት ድርጅት አልነበረም፡፡ይህ ድርጅት የአማራው ሕዝብ ድርጅት ነው ብሎ ደፍሮ ለመናገር በግሌ የተለዩ አቋምና እሳቤ ነው ያለኝ፡፡ለአማራው የቆመ ድርጅት አልነበረም”፡፡
(ለ)”አሁን ይህንን ጥያቄ ለማሥተናገድ ዕውነተኛ ሕዝባዊ ስሜት በማንፀባረቅ በኩል ጅምሮችና ምልክቶች አይቻለሁ፣ይህንን የምናዬው ይሆናል”፡፡
(ሐ) ”እኔም በዚህ ድርጅት አሁን በጉባኤው ሥሣተፍ ጉባኤተኛው በተለይ ደግሞ ወጣቱ ስሜቱን ያንፀባረቀበት ሥለሆነ፣ለዚህ ሕዝብና ወጣት ክብር ብዬ ነው የተቀበልኩት” ብሎ ጀኔራሉ አሥረግጦ ነግሮናል፡፡

**ጀኔራሉ!ከ”ሀ”** እሥከ “ **ሐ**” ከተናገረው ተነሥተን፣ በቀጣዩ ሥራው ይህ አቋሙ ከሌሎቹ የብአዴን ሰዎች ጋር ሊያስማማውም ላያስማማውም፣ አብሮ ሊያስኬደውም ላያሥኬደውም የሚችል ወሳኝና ቁልፍ ነጥብ እንደሆነ መገንዘብ አያዳግትም፡፡ ሥለሆነም እንከታተለው፡፡

ከዚህ በኋላ ወደሥራ ተሰማራ፡፡

-በከሚሴ እነአነግንና የብርሀኑ ጁላን መከላከያ ተብዬው ድባቅ በመምታት፣የትግሬን ተላላኪ ቅማንት ኮሚቴ ተብየውንና የመተከልን ቤኒሻንጉል ሽናሻ ልክ በማሥገባት አማራ አንገቱን ቀና እንዲያደርግና እንዲከበር ያደረገና ያኮራን ጀግና ነው፡፡ **ለአማራ ሕዝብ ቆሞ መሥራትና በአማራ ሥም እየነገዱ ለትግሬና ለጋላ መሥራት ይለያያሉ፡፡**

በተለይ በቤኒሻንጉል ሽናሻ በኩል የበለጠ ፍርሀትን ሥለለቀቀባቸው፣አመራራቸው ”የአማራ ክልል ጀኔራል ኃይለኛ ሥለሆነና ልንቋቋመው ሥለማንችል አርፋችሁ ተቀመጡ እንዳታሥፈጁን” የሚል መልዕክት እሥከማሥተላለፍ እንደደረሰ ይነገራል፡፡

ጀኔራል አሳምነው!” የቀድሞው የክልሉ አመራር ለትነግ(ህዋህት) ታዛዥ በመሆኑ የክልሉን ሕዝብ ጥቅም አሳልፎ ሰጥቷል” ከሚለው የጠነከረ አቋሙ ተነሥቶ ፣ከላይ በ(ለ) “አሁን ይህንን ጥያቄ ለማሥተናገድ ዕውነተኛ ሕዝባዊ ስሜት በማንፀባረቅ በኩል ጅምሮችና ምልክቶች አይቻለሁ፡፡ ይህንን የምናዬው ይሆናል፣” በማለት ከብአዴን/አዴፓ(ኢሕአዴግ/ ብልፅግና) ጋር ለመሥራት ቢነሳም፣ ብአዴን/አዴፓም ከትነግ ተላላኪነት ወደጋላው ተላላኪነት በመለወጡ፣ አሳምነው! ለአማራው ሕዝብ ካለው ፅኑ ተቆርቋሪነት የተነሳ የአማራው ሕዝብ ወገንተኝነቱን አጠንክሮ ገፋበት፡፡

ብዙም ሳይቆይ በክልሉ ሕዝብ በተለይም በወጣቱ ዘንድ ተቀባይነትን አተረፈ፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ከብአዴን ጋር በአቋም አይተዋወቁም ፡፡

በአቋም ሥለማይገናኙ ብአዴኖቹ አምባቸውም ሆነ ምግባሩ ስብሰባ ሲጠሩ አሳምነው የማይገኘው ለዚህ ነው፡፡እነአምባቸውም ጀኔራል አሳምነው ልዩ ኃይል ሲያስመርቅ ያልተገኙትምና ለልዩ ኃይሉም ደመወዝ ላለመክፈል ማዕቀብ ያደረጉበትም ለዚህ ነው፡፡

በአቋም ከተለያዩ ደግሞ (1)አሳምነው!”በአመራሩ ሥብሰባ አይገኝም”፣ (2) የብአዴንን/አዴፓን ሥራ አይሠራም (3)የክልሉን ወጣትና ፋኖን በገንዘብ ይረዳል፣ (5) ወጣቱን በፌስቡክ በማህበራዊ ሚዲያ እያደራጀ የማጥላላት ዘመቻ ያካሂዳል ፣በክልሉ ባለሥልጣናትም ላይ ለማዝመት እያነሳሳብን ነው” የሚሉት ክሶች ዋጋቢስ ናቸው፡፡ ጀኔራል አሳምነው እንኚህን የቀረቡትን የብአዴን “ትችት” ተብዬዎች፣ አድርጓቸው ከሆነ በጣም የነቃ የአማራው ባለውለታ በመሆኑ እና አቋማችንን

በማራመዱ ሙሉ በሙሉ እንደግፈዋለን፡፡ትልቅ ክብርም ይገባዋል፡፡እስከዚህ ድረስ ለአማራው ከሄደ ትልቅ ራዕይ የነበረው መሪ በመሆኑ አድናቆታችን ከፍ ያለ ነው፡፡

ጀኔራል አሳምነው!ተማሮና ተበሳጭቶ በገዛ ፈቃዱ ሥልጣኑን ለቆ እንዲሄድ ያልተቋረጠ ጫና ሲደረግበት እንደነበርም ይታወቃል፡፡

አሳምነው!በወረቀት ብአዴን ውስጥ ያለ ቢመሥልም፣በተግባር ግን ለወገኑ ቆሞ የአማራን ብሔርተኝነት ያጎለበተ፣መቶ በመቶ አቋሙ የአማራ ሕዝብ እንጅ (በሀሰት ትርክት የተገነባ ፀረ አማራ ሥርዓትና ህገ መንግሥት ተሸክሞ፣ከጠላት ጋር አብሮ የአማራን ብሄርተኝነት የሚገድለው) የብአዴን አቋም አለመሆኑን አስመስክሯል፡፡

ለአማራ ብሔርተኝነት በመቆሙ በፀረ አማራዎች ከብአዴን ጀምሮ ትግሬውም ጋላውም ውሀ የማይቋጥሩ ዋይታዎችን በወንጀል ክስ አሥመሥለው ደረደሩበት፡፡

በአሳምነውና እና በብአዴን አመራር መካከል ያለውን የአቋም ልዩነት ከጠቀስኩ በኋላ፣ ጋሎቹና ትግሬዎቹ የአማራ ብሄርተኝነት እንደሚያሥፈራቸው በአቢይ አማካይነት የነገሩንን ልብ ይሏል፡፡ የጀኔራል አሳምነውም በእየግምባሩ ብቅ እያለ ድባቅ መምታትና ልዩ ኃይል ማሠልጠን የራስ ምታት እንደሆነባቸው ገሀድ ነው፡፡

ይህንንም ተከትሎ ጀኔራል አሳምነው እንደሚለው "የጃዊን፣ የቅማንትንና የከሚሴን ጉዳይ የሚያጠና" በሚል በእነዚህ አካባቢዎች የገባ የፌዴራል ኃይል አለ፡፡እኛ ሳናውቀው ወደክልላችን አይገባም ካለ በኋላ "ተከበናል፣ችግሩ ከ500ዓመት በፊት ከነበረው የባሰ ነው" ብሎ አማራው ከጎኑ እንዲቆም ተናገረ፡፡ግን ገብቶን ከጎኑ ቆምን?

ከዚህ በኋላ አቢይ አህመድ አክሱም ሄዶ ከደብረፅዮን ጋር ተገናኝቶ "ምን እንደመከረ"ባናውቅም፣ ወዲያውኑ ወደደሴ ሄዶ አምባቸውና ደመቀ የተገኙበት ሰብሰባ ጠርቶ ካወራ በኋላ "ሥለሥራ አጥነት" ሲጠየቅ "የክልሉን በጀት ልዩ ኃይል ካሰለጠናችሁበት ገንዘብ ከየት ይመጣል" አለ፡፡ቀጥሎም ለምን ጌታቸው አሰፋ ለፍርድ አይቀርብም ተብሎ ሲጠየቅ፣"እናንተም ጋ ሌላው ጌታቸው አሰፋ አለ" ብሎ አለን፡፡

ይህንን ሁሉ ሲል አምባቸውም ደመቀም ኦሮሞና ትግሬ እሥከአፍንጫቸው እንደታጠቁ እያወቁ፣ አንዳችም ነገር አልተነፈሱም፡፡እነኚህ ናቸው የአማራ መሪዎች! አምቦ ሄዶ የጋላን ልዩ ጥቅም የሚያረጋግጥ መሪ ምነው እዚህ ላይ አፉ ታሠረ?

ከዚህ በኋላ ብዙም ጊዜ ሳይቆይ ሰኔ 15ቀን 2011 ዓም የብአዴን ሰዎች እርስ በእርስ እንደተጋደሉና ኤታ ማጆሩም እንደተገደለ፡፡ይህንንም ጀኔራል አሳምነው ያደረገው መፈንቅለ መንግሥት እንደሆነ ቀድመው የተዘጋጁበት የሚመስል የእነአቢይና የእነንጉሱ ጥላሁን ድራማ ተሠራ፡፡

ቀጥሎም በደመ ነፍስ የሚንቀሳቀሱ ሠዎች እርስ በእርሳቸው የሚጣረሱ፣የሚምታቱ፣የማይገናኙና የማይጨበጡ ቲያትር መሠል አሉባልታዎችን "በወንጀል ክስ መልክ" ሲያሰሙን ኖሩ፡፡
ውሸትን በውሸት እያባዙ "ዕውነት" አሥመስሎ ማቅረብ የተለመደበት አገር ኢትዮጵያ መሆኑ ነው እንጅ፣ "ዴሞክራሲና ፍትህ " ባሉባቸው ሀገራት ቢሆን ኖሮ ፣ይህንን የተዘበራረቀና የተለያዩ ሰዎች ንግግር አድምጠው "ዋጋ ቢስ ነው" ብለው "ውድቅ" ያደርጉት ነበር ፡፡አሁን ወደወሳኙ እንሂድ!

.................................................................//.............................................................................

**<u>ትኩረት!</u>** "ግልፅነትና ፍትህ" በጠፋበት አገር ውስጥ ያለው አማራጭ መንገድ፣ "ሀቅን" በገዛ እጅ ማፈላለግ ነው፡፡በመሆኑም  በዚህ አንድ ዓመት ውስጥ የተለያዩ ፀሀፊዎችና ተናጋሪዎች ያበረከቷቸውን በመከታተልና በማጥናት፣ሁኔታውና አካሄዱ ምን እንደሚመስል ከኢንፎርሜሽን ባሻገር የአእምሮን  ሚዛን በማሥተካከል፣እንዲሁም ሁኔታው ከመከሰቱ በፊት የነበሩትን አካሄዶችና ውጣ ውረዶች በማገናዘብ የሆነውን ጠቅለል ባለ ፅሁፍ ማቅረብ የግድ ይላል!

ሥለሆነም ጋሎቹ እነአቢይ ከብአዴን አመራር ጋር  መፈንቅለ መንግሥት እንደተደረገ አሥመስለው ለፈፉ፣

(1)ኤታ ማጆር ሹሙን  ገድለው፣አሳምነው በላከው ሠው እንደተገደለ አስመሰሉት፣

(2) ቀደም ሲል በከሚሴ፣ጃዊና ቅማንት የተሰማራው የአቢይ ቡድን ምርመራውን አጠናቀቀ በሚል ጀኔራል አሳምነውን በዘር ማጥፋት ወንጀል ፈረጁ፡፡

ቅዳሜ ሰኔ 15ቀን  እሥክንድር ነጋ ከአዲስ አበባ ተነሥቶ ባህር ዳር ግብቶ እንደሚያድርና እሁድ ሥብሰባ እንደሚያካሂድ ዕቅድ ሥለነበር፣ጀኔራል አሳምነው ቅዳሜ  ከባልደረቦቹ ጋር የእሁዱን የሥብሰባ ዝግጅት በሚመለከት በሥራ ተወጥሮ እንደነበር ይታወቃል፡፡

በሌላ በኩል  የብአዴን አመራሮች ከእነአቢይ ጋር በመናበብ  ጀኔራል አሳምነውን ከሥራ እንዴት እንደሚያሶጡትና ወደ እሥር ቤት እንደሚወረውሩት  በሥብሰባ  ተጠምደዋል፡፡ከዚህም ተያይዞ አንድም ግርግር ሳይኖር  አድብቶና አዘናግቶ  ጀኔራል አሳምነውን  ይዞ ለማሠር፣ የብአዴንና የአማራ ልዩ ኃይልን መለዮ የለበሰ  የአቢይ አህመድ ቡድን በበቂ ታጥቀውና ተዘጋጅተው ይሠማራሉ፡፡

ጀኔራል አሳምነውም በእርሱ ላይ እንደተዘመተበት ሲነቃ አብረውት የእስከንድርን ዝግጅት የሚያዘጋጁትን ሰዎቹን ይዞ በመሠለፍ እጅ አለምሥጠትን መርጧል፡፡ይህን እሥከአፍንጫው ታጥቆና ቅድመ ዝግጅት አድርጎ  የመጣበትን ኃይል፣የተዋጋውን ያህል ተዋግቶ ሲቆስልና የእርሱን የኃይል ሚዛን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፣የጀግና ልጅ ጀግና ነውና ፣እንደቴዎድሮስ <u>የራሱን ሽጉጥ ጠጥቶ</u> ተሠናብቷል፡፡

ከዚያ በኋላ ቲያትረኞቹ ብአዴኖች ሬሳውን ወስደው ዘንዘልማ ላይ እንደገደሉት በማስመሰል ትንሽ እንኳን ሳይሰቀጥጣቸው ሲጎቱትና ሲዘበቱበት ማዬት ልብ ያደማል፡፡

በዕውነት አንዳንዶች ሊያሳምኑን እንደሚሞክሩት አሳምነው የጀመረው  ቢሆን ኖሮ፣አዲስ ያሠለጠነውን ከ200 በላይ  ልዩ ኃይል በማሰማራት  አንድም አመራር አይተርፍም  ነበር፡፡

(3)አቢይ እንደሚፈራው  ቀድሞ የነገረንን የአማራ ብሔርተኝነት፣ ለማደብዘዝ ከጠቅላላ አገሪቱ ውስጥ የሚገኘውን አማራ፣የአብን አባል ይሁን አይሁን  መርጠው  አሠሩ፣ የገደሉትንም  ገደሉ፡፡

(4)የባልደራስንም በዚህ አጋጣሚ እንዲሁ አሠሩ፡

(5) እሥከዛሬዋ ዕለት ድረስ ቁጥር ሥፍር የሌላቸው አማራዎች  የወታደር ትምህርት ያላቸው ጭምር በእሥር ይማቅቃሉ፡፡ ቁጥሩ የማይናቅ በየትም ቦታ  ያለው  አማራ ይፈናቀላል፣ይደበደባል፣ይገደላል፣

(6) እህቶቻችንና ወንድሞቻችን በወለጋ ተጠልፈው  ቀርተዋል፡፡

በብአዴን አሻሪነትና አማካይነት ለጋሎችና ለትግሬዎች ተጋልጠን መጨፈሪያና መሳለቂያ ባሪያዎች ለመሆን በቃን፡፡ ይህ የማይሠማን ካለን የደነዘዝን ጉዶች ነን ማለት ነው፡፡  ለአማራ ሕዝብ ህልውና

ህይወቱን የሠጠ ጀኔራል አሳምነውን ያህል የጀግና አሟሟት የሞተን ሠው ሬሳውን ከመነተት ጀምሮ እሥከዛሬዋ ዕለት ድረስ እንደፐፋተኛ ለመቁጠር መታገል ተቀባይነት የለውም፡፡አማራ ብለን የተነሳን ሁሉ አቋማችንን እንደገና እንፈትሽ እላለሁ፡፡

ለጀግኖቻችን አገር አማን ሲሆን እንደኳስ ቲፎዞ ድጋፋችን ጣራ ይነካል፡፡ችግር ሲመጣ ግን ከጎን አንቆምም፡፡ለዚህ ነው ታጋዮቻችንን ባስበላን ቁጥር "የእኔም ዕለት ይኸው ነው"በሚል "አዲስ ታጋይ ማፍራት ያልቻልነው፡፡

ትግሬና ጋላ ብአዴን የተባለውን መዥገር በመሣሪያነት ተጠቅመው በዕቅድ፣ <u>አማራን ቀስ በቀስ በጊዜ ብዛት አመናምኖ ከምድረገፅ ለማጥፋት</u>፣ሥርዓት ፈጥረው፣ህገ መንግሥት ቀርፀው 29ዓመት ሙሉ እያፈናቀሉን፣እያባረሩን፣እያደኸዩን፣እየገደሉን እንደሆነ ተግባራቸው ምሥክር ነው፡፡ ሥለዚህ በአማራው ላይ የተጫነ እንጅ ለአማራ የቆመ መንግሥት ሥለሌለን፣"መንግሥት ይድረሥልን" አንበል፡፡ህግና ሥርዓት እንዲሁም ደንብም"በአማራው ላይ የተጫነና አማራን የሚያሳድድ ነው፡፡ይህ እንዲከበር ሳይሆን <u>እንዲቀበር</u> ነው መታገል ያለብን፡፡የትግል መንገዳችን ሁለገብ ወደመሆን ካልተሸጋገረ ዛሬ በምናካሂደው መንገድ አማራውን አናድነውም፡፡

ሥርዓቱ በአጠቃላይ መንግሥቱም፣ህገ መንግሥቱም፣ደንቡም የጋሎችና የትግሬዎች ጥቅም ማሥከበሪያና እንዲሁም የአማራን ሕዝብ ለዕርድ እንዲያቀርብላቸው በጥቅምና በተላላኪነት የያዙት የብአዴን እንጅ የአማራው ሥላልሆነ እምቢተኝነትን እያዳበርን ለራሳችን ህልውና እንታገል፡

ብአዴን! በአማራ ሥም የሚነግድ፣ለአማራ ብሔርተኝነት ፀር ሥለሆነ መወገድ አለበት!

ለአማራ ህልውና ዋሥትናው የአማራ ብሔርተኝነት ነው!

አያሌው ፈንቴ